# ዓመታዊ ሪፖርት

ይህ ዌብ ሳይት ከተጀመረ (ጃንዋሪ 1 ቀን 2003) ስድስተኛ ዓመቱን ይዟል። በተቻለን አቅም የቤተ ክርስቲያና ችንን እምነቷ፣ሥርዓቷ እንዲሁም ታሪኳን በሙሉ እዚህ ዌብ ሳይት ማስፈርባይቻልም ዋና ዋናውን ክፍል ተ ከታይ ምዕመናኖቿ ማወቅ ያለባቸውን ለማሳወቅ የተቻለንን እየጣርን ነው። እንዲሁም ወቅታዊ ትምህርቶችን ፣ የዕለተ ሰንበት ምስባክ፣ ወንጌሉንና ትምህርቱን በማውጣት ምዕመናን አስቀድመው እንዲማሩ እያደረግን ነው። በሳምንት አንድ ጊዜ ተጨማሪ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማውጣት ምዕመናን ወቅታዊ በዓላትን ትርጉማ ቸውን እንዲያውቁ እየሞከርን ነው።

ይህን አገልግሎት መስጠት ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የመጣውም የጎብኝዎች ቁ ጥር በአሁኑ ወቅት በወር ወደ 3 ሚሊዮን ደርሷል። ለጊዜው በዚህ ዌብ ሳይት ላይ ወደ 8000ሺህ ገጽ የሚ ጠጋ ጽሑፍና ከ200 ሰዓት በላይ ስብከትና ዜማዎች ቀርቧል። ከቤተ ክርስቲያናች ቅርስና ትምህርቷ አኳያ ይ ህ ዌብ ሳይት ገና በጣም በጣም ጥቂት የሆነ ትምህርታዊ ጽሑፎችን የያዘ ሲሆን ነገር ግን ብዙ ተጨማሪ ት ምህርቶችና መጻሕፍት ወደፊት ለመጨመር ዕቅድ አለ። አሁንም ብዙ የተወጠነ ዕቅድ ስላለ በዚህ ቅዱስ ተግባር ለመተባበር የምትፈልጉ ካላችሁ ከአምላካችን ዘንድ በረከት የምትቀበሉበት ስለሆነ በምን ዓይነት መርዳት እንደምትችሉ እንድትጽፉልን አደራ እንላለን። በአለፈው ዓመት ሪፖርት ላይ የጀርመንኛና የፈረንሳ ይኛ ቋንቋ ድኅረ ገጾች የተዘጋጁት ከሌላ ዌብ ሳይቶች ጋር በማገናኘት መሆናቸውንና ነገር ግን ዓላማችን ሁሉ ም በውጭ ቋንቋ የተዘጋጁት ጽሑፎች አንድ ዓይነትመልእክት እንዲኖራቸው ነው ማለታችን ይታወሳል።በዚህ ም መሠረት በጀርመን ሀገር በሃኖቨርከተማ የሚኖሩት አቶ ክንፈ ገብረ ኢየሱስ በእንግሊዘኛ ድኅረ ገጽ ላይ የወጡትን፤ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ በስተቀር በሙሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተርጉመው የጀርመንኛው ገጽ የተሟላ እንዲሆን አድርገዋል። ይህ ሥራቸው ብዙዎችን የሚጠቅም፤ የሚያስተምር በመሆኑ ከፍ ያለ ምሥጋና እናቀርባለን። ይኽ ትብብራቸው ወደፊት እንደሚቀጥል ተስፋ እናደርጋለን።እግዚአብሔር አምላክም ጤንነታቸውን እንዲጠብቅ፤ ሕይወታችውን እንዲባርክ እንደፈቃዱምሃሳባቸውን ከግቡ እንዲያደርስላቸው እንመኛለን። ይህ የጀርመንኛ ድኅረ ገጽ ሁሉም የተሟላእንዲሆን የሃይማኖት ትምህርት ዕውቀቱ ያላችሁ፤ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያኑን ገጽ ለመተርጎም ፈቃደኛ የሆናችሁ ወይም ስፖንሰር በመሆን ለማስተርጎም የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ጻፉልን። በተጨማሪም የፈረንሳይኛው ገጽ ከሌሎቹ ጋር አንድ እንዲሆን በመተርጎምም ሆነ ወይም ስፖንሰር በመሆን ለማስተርጎም የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ጻፉልን። እያንዳንዳችን በምንችለው ከተባባርን የበለጠ ለመሥራት እንደምንችል ምንም ጥርጥር የለውም ፤ ስለዚህ እምነታችን እንዲስፋፋ የበኩላችሁን ጥረት እንድታደርጉ እናሳስባለን።

በ2007 የተጀመረው የቆሎ ትምህርት ቤት ከተጠበቀው በላይ ጎብኚዎች ያሉት ሲሆን የጎደሉትን ትምህርቶች በብዛት ተሟልቶ አገልግሎቱ ቀጥሏል።በተለይ የግብረ ዲቁናው ቅዳሴ ትምህርት በደብረ አባይ ዜማ ቀርጸው ላበረከቱልን ነዋሪነታችው በኦሃዮ ለሆኑት የቅዳሴው መምህር አባ ገብረ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን። እግዚአብሔር አምላክ ቃለ ሕይወት ያሰማልን እንላለን። በቅርቡም የመልክዐ ማርያምንና መልክዐ ኢየሱስን ግእዝ አነባበቡን እናቀርባለን።በዚህ ቆሎ ት/ቤት ላይ የተዘረዘሩትን ትምህርቶች አጥንተው ከጨረሱ አቅራቢያዎ ወዳሉት ሊቀ ጳጳስ በመሄድ የሚሰጠውን ፈተና ወስደው ካለፉ የድቁና ሥልጣነ ክህነት መቀበል ይችላሉ።

ቤተ ክርስቲያናችን ዓለም አቀፋዊ ከሆነች ብዙ ዓመታት አሳልፋለች። በተቋቋመችበትም ክፍለ ሀጉራት ለሚገኙ ተከታዮቿ በመጀመሪያ ቋንቋቸው እንዲገለገሉ እየጣረች ነው። አሁንም ከአንዳንድ ምዕመናን በቀረበ ልን ጥያቄና፤ ካህናቶቻችንም የቅዳሴውን አነባብ እንዲለማመዱት በማሰብ አዘጋጅተን በዚህ ዌብ ሳይት ላይ

የመጀመሪያውን ቅዳሴ አቅርበናል። በተጨማሪም በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሙሉ ቅዳሴያት በእንግሊዘኛ እናንት ምዕመናን ትሰሙት ዘንድ እናቀርባለን።

የሰንበት ትምህርት ቤት ከተመሠረተበት ወቅት ጀመሮ የወጡት መዝሙራት ተረስተው እንዳይቀሩ በማሰብ «መዝሙረ ተዋሕዶ» በሚል ርዕስ ተከታታይ ሲዲ ማዘጋጀት መጀመራችን ይታወሳል፤ ትሰሙትም ዘንድ ለቅምሻ ያህል በዚህ ዌብ ሳይት ላይ ወጥቷል። ይህ ተከታታይ የመዝሙር ሲዲ በአለፈው መጋቢት 27 ቀን 2001 በኦክላንድ መድኃኔዓለም <u>የሐመረ ኖኅ ሰንበት ት/ቤት</u> ቁጥር አራትን (የጥምቀት መዝሙራት) በልዩ ሁኔታ አዘጋጅተው አቅርበዋል። ይህን አጋጣሚ በመውሰድ እነዚህን ተሰምተው የማይጠገቡ መዝሙራትን ላቀረቡልን መዘምራንከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባልን። ወደፊትም ተጨማሪ መዝሙራትን እንደሚያቀርቡልን ተስፋ እናደርጋለን ፤ እግዚአብሔር አምላክ ብርታቱን እንዲሰጣቸው፤ ዓላማቸውም ከግቡ እንዲደርስ በጸሎት እናስባቸዋለን።

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ደግሞ ታቅደው ያልተፈጸሙ ነገር ግን ለሚቀጥለው ዓመት ለመሥራት የታቀዱ ናቸው፤

1) ለመናፍቃን መልስ ተብለው የቀረቡትን ወደ ውጭ ቋንቋዎች ማስተርጎምና ማቅረብ፤

2) ተጨማሪ መጻሕፍትን ማቅረብ፤

3) ከአሁን በኋላ የሚቀጥሉት ወራት የሠርግ ወራት ስለሆኑ፤ በቅርቡ ለቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምእመናን የሚከታተሉበት መጽሐፈ ተክሊልን በግእዝ፤ አማርኛ እና እንግሊዘኛ አዘጋጅተን እናቀርባለን።

4) ከበፊት ጀምሮ እያደረግን እንዳለነው በዓላት ከመድረሳቸው ሳምንት በፊት፤ ለበዓሉ የሚባሉትን ዜማዎች፣ ቃለ እግዚአብሔሩን እንዲሁም ትምህርቱን አስቀድመን እናወጣለን። እናንተም አስቀድማችሁ በመለማመድ በበዓሉ ቀን አብራችሁ ከካህናቱ ጋር በማዜም ለበዓሉ ድምቀት ልትሰጡ ትችላለችሁ።

ከሞላ ጎደል የሠራነውና ልንሠራው ያቀድነው ይህ ሲሆን በዚህ ላይ ልትተባበሩና ወይም አስተያየት ያላችሁ ጻፉልን። ዜማዎች ወይም ጠቃሚ ጽሑፎች ካላችሁ ብትልኩልን ደግሞ ሌሎች ወገኖቻችን ሰምተው የሚጠቀሙበት ይሆናል።

እግዚአብሔር አምላክ በዓሉን የሰላም፣ የደስታ እንዲያደርግልን፤ ለሀገራችን ኢትዮጵያ ሰላምንና በረከትን፣ ለሕዝባችንም አንድነትንና ፍቅርን ይስጥልን።

www.ethiopianorthodox.org team!

April 2009

ዌብ ማስተር

<u>በእደ ማርያም እጅጉ ረታ</u>